ግንኙነት በማድረግ ብቻ ብዙ መሄድ አይቻለም:: በደርጉ አካባቢ አንዳንድ ግለሰቦች እየጉሉ መታየት የጀመሩ ይመስላል:: የሰፊውን ሕዝብ ፍላጐት ለማሟላት መፈለግና መቻላቸውን እንጠራጠራለን:: ከኢምፔሪያሊስት አገሮች በተለይም ከአሜሪካ መባሪያ ተጠይቆ በመገባት ላይ እንደሆነ የታወቀ ነው:: የፀረሕዝቡ የሲአይኤ ቡችሎች በአገሪቱ ውስጥ ፀረሕዝብ መረባቸውን ይበልጥ እየዘረጉ አሳፋሪ ተግባራቸውን በማስፋፋት ላይ መሆናቸው ተደርሶበታል:: ሁኔታው በዚህ አኳኋን ከቀጠለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ መውጣቱ ቀርቶ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን የፎሽዝር ቅኝግዛት ቀንበር አገ ደተሸከመ ይቀራል:: ወደወታደር አገዛዝ/ፀረዲሞክራሲ/ እንዳንሄድ ከሚያስጋ ሁኔታ ላይ ባንደርስ አልቀረንም:: ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ የተመለከተው እንዳይደርስ ያሰጋል::

ይህን አደጋ ለመሰወገድ፡እንደዚህ ያለውን አስጊ ሁኔታ ለመቋቋም ሰፊው ሕዝብ በንቃት ሁኔታውን መከታተልና መስራት አለበት፤ መደራጀት አለበት:: የሰፊውን ሕዝብ ትግል የሚያስተባብር ደርግ በቶሎ መቋቋም ይኖርበታል:: ይህ ደርግ የጊዜያዊ ደርግ በሚሰሩት ተከሰለና ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች ያበረታታዋል፤ የሰፊው ሕዝብ ጥቅም የሚጠበቅበትን፡ የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት የሚ ያሟላ ዲሞክራሲያዊ መንግስት በተቻለ ፍጥነት እንዲመሰረት ባለ አቅሙ ይጥራል::

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ይመርጣል፤
አስከመጨረሻው ድረስ ይታገላል፤
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው::